የሰ/መ/ቁ. 46358

የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ብርሃነ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ብርሃን ፀጋዬ - አልቀረቡም ከተባለ በኂላ ጠበቃ ቀረቡ

**ተጠሪዎች**፡- 1ኛ. አቶ ሚካኤል ፍስሐ - ቀረቡ

2ኛ. ናሰው ኮንስትራክሽን - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሽርክና ውል የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው ክስ የተመሰረተው በአመልካች አማካይነት ነው፡፡ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ከአንደኛ ተጠሪ ጋር ያቋቋሙት የሽርክና ውል ፈርሶ የተገዛው ንብረት ተሽጦ እንዲከፋፈሉ እንዲወሰን የሚል ነበር፡፡ አንደኛ ተጠሪ የሽርክና ውል የለንም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡ የአሁን ሁለተኛ ተጠሪ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበትን ኤክስካቫተር ማሽን ባለቤት መሆኑን በመጥቀስ በክርክሩ ገብቶ ለመከላከል ጣልቃገብ ሆኖ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል የተፈረመው ውል የሽርክና ውል እንጂ የአሽሙር ማህበር አይደለም በማለት የሽርክና ውሉ ደግሞ በንግድ ሕግ አንቀጽ 219 /ሐ/ መሰረት አልተመዘገበም በሚል ምክንያት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የከፍተኛው ፍ/ቤትም ይህንኑ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ በአመልካች እና በአንደኛ ተጠሪ መካከል መጋቢት 4/1994 ዓ.ም የተፈረመው ውል

“የአሽሙር ሽርክና ማህበር” መሆኑን አጥብቀው በመከራከር የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ተሽሮ እንደክሱ የዳኝነት ጥያቄ እንዲወሰን አመልክቷል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በግራ ቀኙ

መካከል የተደረገው ውል በሕግ ረገድ የሚኖረው ውጤት ምንድነው? የሚለውን ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ የአንደኛ ተጠሪ ወኪል ታህሣሥ 30/2002 ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት መልስ የሥር ፍ/ቤት ክርክርን አጠናክረው አቅርበዋል፡፡

እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡ አመልካች ከአንደኛ ተጠሪ ጋር የሽርክና ማህበር ያቋቋሙ ስለመሆኑ ለማስረዳት መጋቢት 3 ቀን 1994 ዓ.ም የተፃፈ ውል አቅርበዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የሽርክና ውል የለኝም ይበል እንጂ የቀረበውን ሰነድ ለማስተባበል በሥር ፍ/ቤት ያቀረበው

ክርክርም ሆነ ማስረጃ ስለመኖር የሥር መዝገብ አያስረዳም፡፡ የሥር ፍ/ቤት የቀረበውን ሰነድ ውድቅ ያደረገው ሰነዱ የእሽሙር ማህበር ስለመኖሩ አያስረዳም በሚል ነው፡፡

ከቀረበው ሰነድ መረዳት የተቻለው አመልካችና አንደኛ ተጠሪ የሽርክና ማህበር ለማቋቋም ውል ማድረጋቸውን ነው የውል ሰነድ "የሽርክና ውል ስምምነት" ከሚል በስተቀር ምን ዓይነት የሽርክና ማህበር እንደሆነ አያመለክትም፡፡ ከንግድ ሕግ አንቀጽ 211 መረዳት የሚቻለው የሽርክና ማህበር ጠቅላላ ስያሜ እንጂ የማህበሩን ዓይነት ለይቶ የሚያመለክት አለመሆኑን ነው፡፡ የማህበሮቹ ስያሜ እና ዓይነታቸውን በተመለከተ የንግድ ሕጉ ድንጋጌ ቁጥር 212 በዝርዝር አመልክቷል፡፡

በግራ ቀኝ መካከል አለ የተባለው የሽርክና ማህበር ስያሜው ተለይቶ አልተመለከተም፡፡ ከዚህ መነሻ ሲታይ የሽርክና ውሉ አልተመዘገበም የሚለው የሥር ፍ/ቤት አቋም ምን ዓይነት የሽርክና ውል የሚለውን አልለየም፡፡ ምክንያቱም ምዝገባ የሚያስፈልገው እና ምዝገባ የማያስፈልገው የሽርክና ማህበር በንግድ ሕጉ ተለይቷል፡፡

በግራ ቀኝ ክርክር ይዘት ከመዝገቡም መረዳት እንደተቻለው የአመልካች ክርክር የሽርክና ማህበሩ የእሽሙር የሽርክና ማህበር ስለሆነ ምዝገባ አያስፈልገውም ሕጉ አያስገድድም የሚል ነው፡፡ በአንደኛ ተጠሪ በኩል ያቀረበው ዋነኛ ክርክር እስከነጭራሹም የሽርክና ውል የለም የሚል ነው፡፡ በዚህ ረገድ በአመልካች በኩል የቀረበው ሰነድ

የሽርክና ውል ስለመኖሩ የሚያስረዳ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤትም ተቀባይነት ያገኘ ፍሬ ነገር ነው፡፡ የሽርክና ውሉ የእሽሙር ሽርክና ማህበር ወይንስ ሌላ አይነት ማህበር አቋቁሟል? የሚለውን ለመለየት የሥር ፍ/ቤት በውሳኔው በዝርዝር አላመላከተም፡፡

በሕጉ አገላለጽ ሌሎች የሽርክና ማህበራት ምዝገባ የሚያስፈልግ ሲሆን የእሽሙር ሽርክና ማህበር ግን ምዝገባ አያስፈልገውም፡፡ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 219 ይመለከቷል፡፡

አመልካች ያቀረቡት ሰነድ የሽርክና ማህበር መመሥረቱን የሚያመላክት ሲሆን ባለመመዝገቡ የእሽሙር ሽርክና ማህበር ነው ተብሎ በአመልካች በኩል የቀረበውን ክርክር አንደኛ ተጠሪ በማስተባበል ያቀረበው ክርክር የለም፡፡

ስለሆነም በስምምነት የተቋቋመው ማህበር የእሽሙር ሽርክና ማህበር ስለመሆኑ ከቀረበው ሰነድ ለመረዳት ችለናል፡፡ ስለሆነም የሽርክና ውሉ አልተመዘገበም በሚል ምክንያት የሥር ፍ/ቤት የአመልካቾችን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 15059 የሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 61426 የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካች እና በአንደኛ ተጠሪ መካከል መጋቢት 3 ቀን 1994 ዓ.ም የተደረገው የሽርክና ውል የእሽሙር ክርክር መሆኑ በዚህ ፍ/ቤት ውሳኔ ስለተረጋገጠ የፌ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት የመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ተቀብሎ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 341/1/ መሰረት እንዲመለስ ታዟል፡፡

ግራ ቀኝ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡